# አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል!

(ተስፋዬ ተሰማ)

የማህበረሰብን ግጭት መሰረት በማድረግ ወይም የራስን ብሄር የተጠቂነት ስሜት በማጋጋል የሚቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅት ማለትም ሻብያ ኦነግ ወያኔ እንዲሁም ሌሎች ባለፉት 50 አመታት የኢትዮጵያ እድሜዋ 120 አመት ብቻ ነዉ የተመሰረተችዉም በአፄ ሚኒልክ ተስፋፊነት እያሉ ሲያላዝኑ ቆይተዋል። እኛም ይህ የተሳሳተ አመለካከታቸዉን ከዛሬ ነገ ያሻሽሉታል ወይም እዉነቱን ይረዱታል እያልን እንጠብቅ ነበር ይባስ ብሎ ሰሞንኑን ዘረኞቹ አንዳንድ የኦሮሞ ብሄርተኞች ኢትዮጵያዊ የሚባል ማንነት የለም ማለት ጀምረዉ የበለጠ ግራ እያጋቡን ነዉ። ይህንን ኢትዮጵያዊነት የለም የሚለዉን ነገር በዋነንነት የሚያራግበዉ ዶ/ር ጸጋየ አራርሶ በቅርቡ አዉስትራሊያ ከሚገኘዉ SBS ራዲዮ ጋር ባደረገዉ ቃለ ምልልስ ይህንኑ የኢትዮጵያዊ ማንነት ህልዉና የመካድ አቋሙን በግልጽ አንጸባርቋል፤ ይህንን ነገር ሲናገር ስሰማዉ ይህ ሰዉ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አብረዉት የተማሩት የቅርብ ጓደኞቹ የአእምሮ ጤንነት መታዎክ አለበት እያሉ የሚያዎሩት ነገር እዉነት መሆኑን አረጋገጠልኝ።

ሰወች የፈለጉትን ነገር የማሰብ ያሰቡትንም ነገር በነጻነት የመናገር ዴሞክራሲያዊ መብታቸዉ ነዉ። የሚናገሩትን ነገር እዉነት ነዉ ብለን ሌሎቻችን እንድንቀበለዉና እንድንስማማበት የሚናገሩትን ነገር በማስረጃ እና አሳማኝ በሆነ ምክንያት መደገፍ አለባቸዉ፤ ተምረናል የሚሉት የዘመኑ የኦሮሞ ብሄርተኛ ልሂቃን ይህንን ነገር ከማንም በላይ ይረዱታል። ለግዜዉ እነሱ ኢትዮጵያዊ ማንነት የለም የሚሉትን ነገር በተጨበጠ ማስረጃ እስኪያስረዱን እኛ ኢትዮጵያ ማንነት እንደነበረ፤ እንዳለ እና ወደፊትም እንደሚኖር በማስረጃ እናቅርብላቸዉ። የምንወዳት ሀገራችን ኢትዮጵያ በአለም ረጅም እድሜ አላቸዉ ከሚባሉት ጥንታዊ ሀገሮች ዉስጥ እንደምትመደብ እጅግ በጣም ብዙ ማስረጃወች ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ መጽሀፍ ቅዱስ መንፈሳዉ መጽሀፍ እና የእግዚያብሄር ቃል ከመሆኑም በተጨማሪ የአለም ህዝብ እንደታሪካዊ ማስረጃና ማጣቀሻ ይጠቀሙብታል፤ መጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ ዘኁልቅ መራፍ 12 ቁጥር 1 ላይ እንዲህ ይላል፤

"ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን አግብቷልና ባገባበት በኢትዮጵያዊቷ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ" ይልና እግዚያብሄርም ለምን በሙሴ ላይ ተነሳችሁበት ብሎ ገሰጻቸዉ ይላል፤ ከዚህ ጥቅስ በግልጽ የምንረዳዉ ነገር ኢትዮጵያዊ ማንነት እንደነበረ ነዉ፤ ወደ ዘመን ቀጣሪዉ ስንሄድ ደግሞ ሙሴ በምድር ላይ የነበረበት ዘመን እየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ 1393 (አንድ ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ሶስት) አመት በፊት ነዉ፤ እየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ ደግሞ በፈረንጆች ከቆጠርን 2016ኛ የልደት በአሉን ልናከብር ትንሽ ቀናት ነዉ የቀሩን፤
1393 + 2016 = 3,409 መሆኑ ነዉ

ስለዚህ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንደነበረችና እንዳለች ኢትዮጵያዊ የሚባል ማንነትም እንደነበረና እንዳለ የኢትዮጵያ እድሜዋ ደግሞ የኦሮሞ ብሄርተኞች ወይም ሌሎች ጸረ ኢትዮጵያዉያን ግለሰቦች እና የፖለቲካ ድርጅቶች እንደሚሉት 120 አመቷ ሳይሆን በትንሹ 3,409 (ሶስት ሺህ አራት መቶ ዘጠኝ) አመት በላይ እድሜ ያስቆጠረች ጥንታዊ ሀገር መሆኗን እንኳን ሰዉ እግዚያብሄርም የመሰከረዉ መሆኑ ነዉ፤

አብዛኛዉ የኦሮሞ ብሄርተኛ ልሂቃን የራሳቸዉ የሆነ ታሪክ የላቸዉም። በየጊዜዉ የሚፈላሰፏትን አስቂኝ የፈጠራ ታሪክ የሚደግፉበት ምንም አይነት ማስረጃም አያቀርቡም። ሌላ ሰዉ ደግሞ በተጨበጠ እና በአሳማኝ ማስረጃ እንዲሁም በምክንያት ሲከራከሯቸዉ እዉነቱን ለመቀበል ድፍረት ስለሌላቸዉ እዉነቱን ሁሉ የደብተራ ታሪክ እያሉ ያጣጥሉታል። ካልሆነም የኦሮሞ ፎብያ እያሉ እዉነቱን የሚነግራቸዉን ሰዉ ለማሸማቀቅ ይሞክራሉ። የሚገርመዉ ነገር አንዳንድ የኦሮሞ ብሄርተኞች ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊ ማንነትን ሲዘልፉና ሲዋርዱ ኢትዮጵያ ፎቢያ

እንላቸዉም፤ በአፄ ሚኒሊክ ላይ የማያቋርጥ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሲነዙ ሚኒልክ ፎቢያ አለባቸዉ ብለን አናዉቅም፤ አማራና ትግሬን ሲያወግዙና ሲሳደቡም የአማራና ትግሬ ፎቢያ አለባቸዉ ብለን አዉርተን አናውቅም፤ እነሱ ግን ስለነሱ እዉነተኛ ነገር ቢነገር ወይም እነሱ ስለሌላዉ የሚናገሩት ነገር መሰረት እንደሌለዉ በማስረጃ አስደግፈህ ብትናገር ኦሮሞ ፎብያ አለባችሁ በማለት ክርክሩን ከምክንያታዊነት ወድ ስሜታዊነት በመዉሰድ ነገሩን ሁሉ ማለቂያ ወደሌለዉ ጭቅጭቅ ይወስዱታል። በኢትዮጵያዊነታቸዉ የሚያምኑ ኦሮሞዎች  የኦሮሞ ብሄርተኞች በየግዜዉ የሚፈለፍሉትን የፈጠራ ታሪክ አልቀበል ሲሏቸዉ ጎበና እያሉ አንገታቸዉን ለማስደፋት ይሞክራሉ።

አሁን ባለችዉ የኢትዮጵያ ምድር ላይ ለዘመናት የኖሩ ኢትዮጵያዊ የሚባሉ ዜጎች አሉ.። ሀገራችን ኢትዮጵያም እረጅም እድሜ የኖረች ጥንታዊ ሀገር ናት። ደግሞም የራስዋ የሆነ ስልጣኔ የነበራት እና ያላት ሀገር መሆንዋን በአለም የታወቁ የሰዉ ልጅ ስልጣኔ አጥኝዎች “Civilization scholars” ይመሰክሩላታል፤ የሀርቫርድ የአለም አቀፍ ጉዳዮች ማእከል ዳሬክተር በመሆን ከግማሽ ምእተ አመት በላይ የሰራዉ ታዋቂዉ የፖለቲካ ሳይንቲስት Samuel Huntington በ 1993 ዓ.ም እዉቅናን ባስገኘለት “The Clash of Civilization and the Ranking of World Order” በተባለዉ መጽሀፉ ላይ በኢትዮጵያ ስለነበረዉ ጥንታዊ ስልጣኔ እንዲህ ይላል፤

በተለያዩ ቦታ እና በተለያዩ ጊዜ ተነስተዉ የነበሩ የሰዉ ልጅ ስልጣኔን በማጥናት የሚታወቁ ዋና የስልጣኔ አጥኝ ምሁራን Major Civilization scholars በአፍሪካ ዉስጥ ምንም አይነት ስልጣኔ አልነበረም. ኢትዮጵያ ግን የራስዋ የሆነ ስልጣኔ ያላት አገር ናት ብለዉ ያምናሉ ብሏል፤ ከዚህ የምንረዳዉ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንደነበረች፤ ኢትዮጵያዊ የሚባል ማንነት እና የዜጎቹ ስልጣኔም መኖሩን ነዉ። እንደልማዳቸዉ ይህንንም የደብተራ ታሪክ እንዳይሉ ግን እሰጋለሁ።

የኦሮሞ ብሄርተኛ ልሂቃን ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የለችም የሚሉትን አዲሱን ፈሊጣቸዉን ተሰብስበን ከጓደኞቻችን ጋር ስናወራ በዚህ አባባል የተናደደ ወዳጃችን እንዲህ አለ “ኢትዮጵያ የለችም የሚሉት የኦሮሞ ካድሬዎች ሳይፈጠሩ ኢትዮጵያ ነበረች፤ እነሱንም የሚፈለፍላቸዉ ኦነግ የሚባልዉ ድርጅት ሳይመሰረት ሀገራችን ኢትዮጵያ ነበረች፤ ኦነጎች ኢትዮጵያን በመስፋፋት ፈጠሯት እያሉ የሚወነጅሏቸዉ አፄ ምኒልክ ሳይወለዱም ኢትዮጵያ ነበረች፤ እራሳቸዉ ኦሮሞዎች አሁን በኢህአዴግ ጊዜ ኦሮሚያ ተብሎ በተከለለዉ ክልል ከመምታጣቸዉና ከመስፋፋታቸዉ  በፊት ኢትዮጵያ ነበረች” አለ። በታሪክ እንደሚታወቀዉ የዛሬ 487 (አራት መቶ ሰማንያ ሰባት) አመት በ1529 ናዝሬት አካባቢ (በአሁኑ በኢሀዴግ አጠራር የኦሮሚያ ክልል) በግራኝ አህመድና በአፄ ንብለድንግል በሚመራዉ የኢትዮጵያ ጦር መካከል ብዙ ህዝብ ያለቀበት ከባድ ጦርነት ተደርጎ ነበር በዚህን ግዜ ኦሮሞዎች በቦታዉ አልነበሩም እንዲያዉም ናዝሬት የሚለዉ ስም ተቀይሮ ወደጥንቱ ስሙ ይመለስ ከተባለ አዳማ ሳይሆን ሸንብራ ኩሬ ነዉ መባል ያለበት ብለዉ የሚያምኑ በጣም ብዙ ሰወችም አሉ።

ይሁንና ብዙ ሌላ በጣም ብዙ እዉነተኛ ማስረጃዎች ጠቅሰን ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንደነበረችና ኢትዮጵያዊ የሚባል ማንነትም እንደነበረ የኢትዮጵያ ስልጣኔ የሚባልም እንደነበረ ሀገራችን ጥንታዊ ከሚባሉት ሀገሮች እንደምትቆጠር ወይም እንደምትመደብ መናገር ስንጀምር መስማት የማይወዱት የኦሮሞ ልሂቃን “አሁን ያለችዉ ኢትዮጵያ” የሚል  ሌላ የሞኝ ክርክር ያመጣሉ

አንድ ሀገር በግዜ ሂደት ግዛቱ ሊሰፋ እና ሊጠብ ይችላል፤ ይህ ማለት ግን የሀገሩን ሀገርነት አያሳጣዉም፣ የዚህ አይነት ክርክር ደግሞ የትም አያደርስም፤ ለምሳሌ አሜሪካን USA የተባለችዉ ታላቅ ሀገር የዛሬ 240 አመት ስትመሰረት 13 ግዛት ብቻ ነበራት፤ በአሁኑ ሰአት 50 ግዛቶች አሏት. የመጨረሻዋ ወደ አሜሪካ የተጠቃለለችዉ ሀዋይ ወደ አሜሪካ ግዛትነት ከተጠቃለለች ገና 59 አመቷ ነዉ አንድ ሰዉ አሜሪካ ስንት አመቷ ነዉ ተብሎ ሲጠየቅ አሁን ያለችዉ አሜሪካ ገና 59 አመቷ ነዉ እያለ አይጃጃልም፤ ምክንያቱም የሀገር እድሜ የሚቆጠረዉ

በተመሰረተበት እንጅ የመጨረሻዉ ግዛት በገባበት አደለምና። የኛም ሀገር ኢትዮጵያ እንደ ሌሎች ሀገሮች ሁሉ እድሜዋ የሚቆጠረዉ ከተመሰረተችበት እንጅ የመጨረሻዉ ግዛት በገባበት አደለምና። በዚህ ስሌት ከሄድን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ከተገነጠለች እና ያሁኑን ቅርጿን ከያዘች 25 አመት በመሆኑ የኢትዮጵያ እድሜም 25 አመት ነዉ ማለት ነዉ። ሀገራችን አብዛኛዉ በአለም የታወቁ ስለሀገር የሚያጠኑ የ Nationalism scholars አንድ እዉነተኛ ሀገር ወይም ደግሞ Organic Nationalism ለመባል ማሟላት አለበት የሚባለዉን ብዙዉን መስፈርት የምታሟላ እዉነተኛ ሀገር ናት። ታላቁ የፖለቲካ ፈላስፋ አርስቶትል አገር የሚፈጠረዉ ከቤተሰብ ቤተሰብ እየሰፋ ሲመጣ ጎሳ ጎሳዎችም እየጨመሩ ሲመጡ ነዉ ይላል። ይህም ማለት ኢትዮጵያ እንደሌሎች የአለም ሀገራት የተሰራችዉ በዚሁ ሂደት ነዉ።

አዉቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም እንደሚባለዉ ጽንፈኞቹ የኦሮሞ ብሄርተኞች ስለሚክዱት እንጅ አሁን ያለችዉ ኢትዮጵያ እንድትመሰረት ከቅኝ ገዥዎችና ከወራሪ ጠላቶች ተጠብቃ እንድትኖር እንደሌሎች ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻቸዉ ሁሉ የኦሮሞ ታላላቅ ጀግኖች ብዙ የደምና የህይወት መስዋትነት ከፍለዉ ኢትዮጵያን እዚህ አደረስዋታል። እነዚህ ሰወች በብዙ ማስረጃ የተረጋገጠዉን የኢትዮጵያ ሀገራችን እና ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን በፈጠራ ወሬና ፕሮፓጋንዳ ብዛት አጥፍተዉ ለራሳቸዉ አእምሮ እንጅ በሌላ በሰዉ ልጅ ታርክ ዉስጥ ተፈጥሮ የማያዉቅ አዲስ ኦሮሚያ የሚባል ሀገር አለ ብለን እንድናምን የሚያደርጉትን ጥረት ሳይ በጣም ይገርመኛል። እዉነተኛ ታሪክን አጥፍቶ ሌላ የፈጠራ ታሪክ ለመፍጠር መሞከር በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ እንደሞዴል ከሚቆጥሯት አዲሷ አገር ኤርትራ መማር ይችላሉ። በነገራችን ላይ ኤርትራ ነጻ ወጣች ከተባለ በኋላ በታሪካቸዉ አይተዉት የማያዉቁት በለየለት አምባገነን መገዛት ከጀመሩ 25 አመት አስቆጥረዋል፤ በዚህም ምክንያት ይመስላል አዲሱ የኤርትራ ትዉልድ "ነጻነት እንደዚህ ከሆነ ባርነት አልነበረም" ብሎ መናገርም ጀምሯል።

ታሪክን አጥፍቶ አዲስ ታሪክ መፍጠር ከባድ ነዉ ወደሚለዉ ሃሳቤ ስመለስ ኤርትራ ዉስጥ አንድ ስብሰባ ላይ አንድ አስተዋይ ሰዉ ተነስቶ የሻብያን ባለስልጣናት ብዙ ግዜ የኤርትራ ታሪክ የሚቆጠረዉ ሻብያ ነጻ ካወጣት በኋላ ያለዉ ነዉ፤ ጀግናዉ አሉላ አባነጋ ወራሪዉን 500 የጣሊያን ወታደር የጨረሱት እዚሁ ኤርትራ ዉስጥ ነዉ እና ይህ ታሪክ የኛ ታሪክ ክፍል አደለም እንዴ ብሎ በመጠየቁ መታሰሩን ሰምቻለሁ።

እምዬ ምኒልክ ሳይወለዱ ኦሮሞዎች ያሁኑን የአማራ ክልል የተባለዉን ጎጃምን ጎንደርን ወሎን እና ሸዋን ሲገዙ በነበረበት ግዜ የዛሬ 219 (ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ) አመት ነጻና ኩሩ ኢትዮጵያዉያኖች እዚህ አሜሪካን አገር ስለፈጸሙት አኩሪ ታሪክ ልናገርና ነገሬን ልጨርስ። አጼ ሚሊልክ የተወለዱት በ 1844 ዓም ነዉ፤ ይህ ታሪክ ደግሞ የተፈጸመዉ እሳቸዉ ከመወለዳቸዉ ከ36 (ሰላሳ ስድስት) አመት በፊት በ 1808 ኒዉዮርክ ዉስጥ ነዉ። እነዚሁ ኢትዮጵያዉያን ነጋዴዎች ለስራ መጥተዉ እዚህ ነዉዮርክ ይኖሩ ነበር። በወቅቱ ደግሞ አሜሪካን አገር ጥቁርና ነጭ አብረዉ ትምህርትቤት አይሄዱም አብረዉ ምግብ ቤት አይመገቡም፤ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ እንኳን ነጭና ጥቁሮች የሚቀመጡበት የተለያየ ቦታ ነበር። ኩሩና በነጻነት መኖር የለመዱ ኢትዮጵያዉያን ወደቤተክርስቲያን ሲሄዱ ጥቁር የሚቀመጥበት ቦታ እንዲቀመጡ ሲጠየቁ በእግዚያብሄር ቤት ጥቁርና ነጭ ብሎ ነገር የለም ሁላችንም እኩል ሰወች ነን አብረንም የማንቀመጥ ከሆነ እኛም የራሳችን ቤተክርስቲያን መስርተን እግዚያብሄርን በነጻነት እናመልካለን ብለዉ ሌሎች ጥቁር አሜሪካዉያንን ይዘዉ አቢሲኒያ ባፕቲስት ቸርች የተባለዉን ታዋቂዉን የጥቁር ቤተክርስቲያን ለመጀመሪያ ግዜ ከፈቱ። ከዚህ ታሪክ በግልጽ እንደምንረዳዉ ኢትዮጵያዊነት ነበረ በራስ የመተማመንና የነጻነት ስሜት የነበራቸዉ ኢትዮጵያኖችም ነበሩ፤ ይህ የነጻነት ስሜት ደግሞ ለኛ ብቻ ሳይሆን ለጥቁር ዘር በሙሉ ምሳሌ ሆኖብዙ ታላላቅ ስራዎችን ሲሰራ ኖሯል።

እንደኔ እንደኔ የኦሮሞ ብሄርተኞች ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ያላቸዉን የተዛባ መረዳት ቢያስተካክሉ ይበጃቸዋል እላለሁ። በመንግስትና በሀገር (በኢትዮጵያዊነት) መካከል ያለዉን ለዩነት በትክክል ቢረዱት ጥሩ ነዉ። ኢትዮጵያን አፍርሰን ኦሮሞያ የሚባል አዲስ ሀገር እንመሰርታልን የሚለዉን

የቀን ቅዠታቸዉን ቢያቆሙ መልካም ይመስለኛል፤ ኢትዮጵያ በታሪክ ዉስጥ በተደጋጋሚ በሀገርም ዉስጥም ይሁን ከዉጭ በመጡ ሀይሎች ፈታኝ ወቅቶችን አሳልፋ እዚህ ደርሳለች፤ ከ3000 (ሶስት ሺህ) አመት በላይ ያላት ጥንታዊቷ ኢትዮጵያን ትፈርሳለች ብሎ ከማሰብ ኢህዴግ ጠፍጥፎ የሰራዉ የ25 አመቱ ኦሮሚያ ክልል ይፍርሳል በሎ ማሳብ ጤነኛና ምክንያታዊ አስተሳሰብ ይመስለኛል። እኔ በግሌ በብሄር ላይ የተመሰረተ ክልልም ይሁን የፖለቲካ ድርጅት ለወደፊቷ ኢትዮጵያ አደጋ እንጅ ምንም ጥቅም ያመጣል ብየ አላምንም። ለነገሩ ኢትዮጵያ ሳትፈርስ ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ የተነሱት በብሄር የተደራጁት ኦነግ ሻብያና ኢህዴግ ቀድመዉ እየፈራረሱ ይመስላል። ምንም ይሁን ምንም ኢትዮጵያ አትጠፋም ኢትዮጵያዊነትም ለዘላለም ይኖራል።

መጽሀፍ ቅዱስ በትንቢተ ኤርምያስ መእራፍ 13 ቁጥር 23 ላይ እንደሚነግረን ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ነብርም ዥንጉርጉርነቱን አይተዉም።

ቸር ይግጠመን
ተስፋዬ ተሰማ
ከሜሪላንድ አሜሪካ